# ያ ትውልድ

ቀን ፡ ጥር ፳፪ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም. (January 30, 2014)

## «ያ ትውልድ ተቋም» ቤተ መረጃ

*ከ«ያ ትውልድ ተቋም» የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ*

«ያ ትውልድ ተቋም» በጀመርነው የኢትዮጵያ የትግል ታሪክ መረጃ ማሰባሰብ መሠረት በያ ትውልድ ድረ ገጽ http://www.yatewlid.com ወይም http://www.yatewlid.org ተጨማሪ የተለያዩ ሠነዶችና የሰማዕታት ስም ማስገባታችንን ለመግለጽ እንወዳለን። በዚህም መሠረት፦

### *የተለያዩ ሠነዶች*

- በተለይ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1970 ዓ.ም. በአለው ወሳኝ ትግል ወቅት ወጥተው የነበሩ መጣጥፎችን የማሰባሰቡ ሂደት በመቀጠል በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በጊዜው ወጥተው የነበሩ የዴሞክራሲያ ዕትሞችን አንድ መቶ ሰማንያ ሦስት (183) ዕትሞች ተካተዋል።
- መልዕክተ ኢሕአፓ (በኢሕአፓ-ህትመት-መልዕክተ ኢሕአፓ ክፍል) 49 ዕትሞች ገብተዋል
- ላብ አደር (በኢሕአፓ-ህትመት-ላብ አደር ክፍል) 7 ዕትሞች ገብተዋል
- የኢሕአፓ የድሮ መዝሙሮችና ግጥሞች (በኢሕአፓ-መዝሙር ክፍል) በድምጽ ቅጂ ተካተዋል ምሳሌ ታዋቂው የኢሕአፓ መዝሙር ለዘመናትና ሌሎች። በተጨማሪ በዚሁ ክፍል ከያ ትውልድ ወገኖች የተለያዩ ግጥሞች ለምሳሌ፦ ፀጋዬ ደብተራው ግንባርህን አሳያቸው፣ የኃይሌ ኀመራው ስብስቦች፣ አልተለየሽኝም እሳቱ ከበደ፣ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት ወዘተ ተካተዋል።
- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያ ኃይሎች ኀብረት (ኢዴኃኀ) ሠነዶች (በፖለቲካ ድርጅቶች-ህብረት-ኢዴኃኀ ክፍል) የተገኙት ተካተዋል።

### *የቀይ ሽብር ሰማዕታትን በተመለከተ*

በያ ትውልድ ተቋም ድረ ገጽ የተካተቱት ከሦስት ሺህ በላይ የሰማህታት ስም ዝርዝር እንደተጠበቀ፦

- በጎንደር 880
- በጎጃም 270
- በትግራይ 318
- በሐረር 261
- በአዲስ አበባ ከፍተኛ 1 (96)፣ ከፍተኛ 3 (155)፣ ከፍተኛ 11 (93)፣ ከፍተኛ 12 (94) ከፍተኛ 15 (167) በጠቅላላው 605 ሰማዕታት ስም በማስገባት በፊት ከነበረው ከፍ ብሏል።

በጠቅላላው ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ አራት ዘጠኝ (2334) የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወገኖቻችን ስም በፊት ከነበረው በተጨማሪ ተካቷል።

## *የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጭዎችና ተሳታፊ*

በደርግ የአንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ዕቅድ አውጪዎች፣ አስፈጻሚና ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር በአለው አገዛዝ ከተሰጣቸው የፍርድ ውሳኔ ጋር በአዲስ አበባ በየከፍተኛው እና በክፍለ ሀገር በየአውራጃውና ወረዳው መሠረት በያ ትውልድ ድረ ገጽ (የቀይ ሽብር ተሳታፊዎች ክፍል) ተካቷል። በዚሁ መሠረት ከታች በዝርዝር የተቀመጠው ቁጥር አጠቃላይ የአንድ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና (1190) ስም ዝርዝር፣ ኃላፊነታቸውንና የተሰጣቸውን ፍርድ አካቶ ተካቷል።

| በደርግ የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጪዎችና ተሳታፊዎች | ብዛት |
|---|---|
| በደርግ የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጭዎች | 73 |
| በደርግ የቀይ ሽብር ፖሊሲ አስፈጻሚዎች | 96 |
| **በደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊዎች** | **ብዛት** |
| አዲስ አበባ በ25ቱ ከፍተኛ | 284 |
| በሸዋ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 232 |
| አሩሲ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 66 |
| ወሎ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 111 |
| ትግራይ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 57 |
| ጎንደር የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 49 |
| ጎጃም የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 29 |
| ከፋ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 36 |
| ሲዳሞ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 50 |
| ሐረርጌ የተለያዩ አውራጃና ወረዳዎችን ጨምሮ | 28 |
| ወለጋ | 2 |
| ኢልባቡር | 3 |
| ጎሙጎፋ | 9 |
| ባሌ | 26 |
| ኤርትሪያ | 2 |
| በተለያዩ መስሪያቤቶች | 37 |
| **ጠቅላላ** | **1190** |

በሀገራችን ከነበሩት አገዛዞች በአስከፊነቱና በገዳይነቱ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም ይመራ የነበረው የደርግ አገዛዝ ነው ብለን እናምናለን። በዚህ የደርግ አገዛዝ አንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ተብሎ በሚታወቀው ዘመን ለተሰዉ ወግኖቻችን ዋና መታሰቢያነቱን ይዞ የሰማዕታቱን ስም እንዳካተተ ሁሉ በጊዜው የነበሩት የግድያው አቀናባሪዎችና ተሳታፊዎች ስም መውጣቱ ከታሪክ አንጻር አስፈላጊ ነውና በተቀናበረ መልኩ አቅርበንላችኋል።

የሀገራችንን የዴሞክራሲና የነፃነት የትግል ታሪክ ማሰባሰብና በተጀመረው ያ ትውልድ ድረ ገጽ መልሶ ለሕዝብ ማቅረብ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው «ያ ትውልድ ተቋም» በድረ ገጹ የተካተቱትን በመመልከት በኢሜል አድራሻችን አስተያየታችሁን ትሰጡን ዘንድ በትህትናና በአክብሮት እንጠይቃለን።

## ***ምስጋና***

- የኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ዕትሞችን እናገኝ ዘንድ ለተባበራችሁን የያ ትውልድ ወገኖች የከበረ ምስጋናችን በዚህ አጋጣሚ ይድረሳችሁ እንላለን።
- የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወገኖቻችንን ስም ዝርዝርና የተገኘውን ፎቶ በማጣራት ለምትልኩልን ተባባሪ ወገኖች፤ ሙታን ወገኖቻችንን ከፍ ከፍ አርጋችኋልና በስማቸው ምስጋናችንን ተቀበሉን።
- «ያ ትውልድ ተቋም» በቅርቡ ለአንዳንድ ወገኖቻችን የዕርዳታና የትብብር ጥሪ በአቀረብነው መሠረት ፈጣን መልስ ለሰጣችሁን ወንድምና እህቶቻችን ከበሬታችን የላቀ ነው። አሁንም በማንኛውም መንገድ «ያ ትውልድ ተቋም»ን ለመተባበርና ለመርዳት ፍላጎት ላላችሁ ኢሜል አርጉልን፤ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ፍላጎቱ ላላችሁ በድረ ገፃችን ላይ የ PayPal Account ስላስቀመጥን በመጠቀም መርዳት እንደምትችሉ በዚህ አጋጣሚ ማሳወቅ እንወዳለን።

ያ ትውልድ ተቋም በቀጣይነት በአለው አቅም መሠረት ተልዕኮውን እየተውጣ ይገኛል። አሁንም ወደፊትም የተለያዩ የያ ትውልድና ተዛማጅ መረጃዎች ያሏችሁ በመላክ ትተባበሩን ዘንድ በአክብሮት እየጠየቅን በቀጣይነት በመሠራት ላይ ያለውን የያ ትውልድ ድረ ቀጣይ ሥራ እንደተጠናቀቀ እናሳውቃለን።

**የያ ትውልድን አኩሪ ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ ሁላችንም እንተባበር።**

<<ያ ትውልድ ተቋም>> ለያ ትውልድ መታሰቢያነት።
ያ ትውልድ ተቋም

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org